# ሰሞኑን በፓል ቶክ
## ክፍል 5

ከበልጅግ አሊ

1ኛ. እንደተለመደው ሱሴንም ለመወጣት ቢቻልም ለመማር ስል እንደገና በየፓልቶኩ ስዘዋወር ነበር።በዚህ ሳምንት የደደቦች ሸንጎ የስድብ መለኪያዬን ስመለከተው ሲሰደብ የከረመው የቀድሞውን አጋፋሪያቸው የነበረውን ቪቫ ሚኒሊክ በመባል የሚታወቀው ነው። እሱም የጠፋ ስሜን አድሳለሁ ብሎ አንድ ሌላ ክፍል ከፍትዋል። የሚገርመው ይህችም ወሬ ሆና የወያኔ የሆነው ድህረ ገፅ ዓይጋ ፎረም ይህን ይዞ ጮቤ ሲረገጥ ነበር። ይህ ከደደቦች ሸንጎ የተነጠለው አጋፋሪ ክፍሉን ጥሎ በመውጣቱ ምክንያት ክፍሉ ከሌሎች ተባብረን እንስራ፣ መሳደብ እናቁም የሚለው ወገን እየመነመነ እየመጣ መሆኑን አንዳንድ „የፓልቶክ ኤክስፐርቶች“ ይናገራሉ ።

2ኛ. በሌላው የፓልቶክ ክፍል ለቃለ መጠይቅ የቀረቡት አቶ አረጋዊ በርሄ ናቸው። ጥሩ የሆነ ትምህርታዊ ቃለመጠይቅ ነበር ለማለት ይቻላል። ስለድርጅታቸው ብዙ ገለፃ ሰጥተውናል።ነገር ግን አንድ እሳቸው ያቀረቡት ሃሳብ እኔን ሊያሳምነኝ ያልቻለው የድርጅቶችን ውህደትን በሚመለከት እንደሚደግፉ የገለፁት ነው።የድርጅቶች ውህደት በጣም ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባ ነው እላለሁ።ውህደት በችኮላ ወይም ለይሰሙላ ሊሆንም አይገባም። አሁን እንኳ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ስንት ድርጅቶች ተዋህደው እንደነበር ስናስታውስ እውነት ውህደቱ ተሳክቶአል?ብለን መጠየቅ ይገባናል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ኃይሎች ህብረት ወስጥ ያሉ ደርጅቶች ለመዋሃድ በቂ ናቸው? ለመሆኑ በህብረት የሚሰሩት አልቆ ነው ወደ ውህደት ማሰብ የተጀመረው? ወይስ የመድህን-ኢደፓ አይነት ህብረት ለመመስረት ተፈልጎ ነው? አንድ በውጭ ያለ የመድህን አባል ስለ መድህን-ኢደፓ ውህደቱ ትልቅነት ሲነግረኝ የደረቀ ከንፈሩ ሳይርስ ነው ውህደቱን በተለይም ልደቱን ( ክደቱን ) መሳደብ የጀመረው። ታዲያ በሁለቱ ድርጅቶች መካከል የተፈጠረው ውህደት እንደ ታላቅ ገድል ለአንድ ሰሞን ስናናፍሰው እንዳልከረምን፤ለልደቱ ለወያኔ መሸጫ ዋጋውን ጨመረለት እንጂ ያመጣው ጥቅም የለም። ኢዴኃህ ቸኩሎ ውህደት ቢያደርግ ኖሮ በየነ ጴጥሮስና መረራ ጉዲና የሚመሩት ድርጅት ከህብረቱ ውሳኔ ውጭ ወያኔ ፓርላማ ሲገባ ውህደቱ ፈርሶ ነበር። እኔ በበኩሌ ጠንካራ ህብረት ከውህደት በፊት ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ። ይህ ብቻ ሳይሆን በፀረ ወያኔነት የተፈጠረ ህብረት ለውህደት በቂነት አለው ብዬ አላምንም። የአላማ ወይም የአመለካከት አንድነት ከሌለ ውህደት አይሰምርም።ውህደት እንዲሳካ የሚዋሃዱት ክፍሎች የኛ ተለያይቶ መገኘት የድርጅቶች ድግግሞሽ እንጂ በምንም ልዩነት የለንም የሚል አመለካከት ሲይዙ ብቻ ነው።ከቱሉ ፎርሳ እስከ ሞአንበሳ ድረስ ተብሎ በፀረ ወያኔት የተቋቋመው ህብረትን ወደ ውህደትን መለወጥ አስጊና አደገኛ እንጂ ጠቃሚነት የለውም።

3ኛ. ሰሞኑን የወያኔን የምዕተ አመት ዝግጅትን በሚመለከት አንዳንድ ግለሰቦች በፓልቶክ የወሰዱት አቋም በጣም የሚገርም ነው።በተለያዩ ግዜያቶች የተለያዩ ግለሰቦች በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ወያኔ ጋር እንድንታረቅ ተቃዋሚ መስለው እኛው ጋር ተቀምጠው የሚለምኑን እናያለን። ከዚህ ቀደምም ወያኔ ሶማሊያ የገባ ሰሞን እንደዚሁ ከኢትዮጵያ ወታደር ጋር መቆም አለብን ተብሎ ተሞክሮም ነበር።አሁን ደግሞ ለምዕተ አመቱ ዝግጅት ተባባሪ ለመሆን በእናት አገራችን ስም ስንለመን ነው የከረምነው።የሚያቀርቡት ምክንያት የሚያስቅም የሚያሳዝንም ነው። ሚሊኒየም አንድ ግዜ በሽህ አመት የሚመጣ ስለሆነ መሳተፍ አለብን ፤የሃገራችንን ኢኮኖሚ በበዓሉ ምክንያት ሲያድግ የሃገራችን ህዝብ ይጠቀማል፣ወያኔ ሚሊኒየምን በማመኑ አገራችን የመቶ አመት እድሜ ነው ያላት የሚለውን አሳብ በመቀየሩ ሚሌንየምን ማክበር

ያስፈልጋል፣ የሚል የሚያስቅ ምክንያት ነበር የሚያቀርቡት።በጥሩ ሁኔታም ይህንን በአሽሙር ወያኔን ለመርዳት የሚደረግ ጥረት ቆራጦች ቀን ተሌት ተከራክረው እውነቱን አስረግጠዋል። ለመሆኑ በግንቦቱ ምርጫ የሞቱት የአይናቸው ሳይፈስ ይህ መታሰቡ ምን ይባላል?በወያኔ ፋሽሽታዊ ጥይት ህይወታቸውን የአጡት በሚሊየኒይም መሳተፍስ አይፈልጉም ወይስ አይገባቸውም ነበር? ብዙ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል።

4ኛ. በሌላ በኩል አንድ ጥያቄ ሁልግዜ ላነሳው እወዳለሁ።ፓልቶክ ሱስነቱ ምን ያህል ነው ? ለሁላችሁም የምጠይቃችሁ ቢኖር የገዛ ልጁን ያልወደደ አገሩን ይወዳል ? 24 ሰዓት በፓልቶክ ውስጥ የምናያቸው እናቶችና አባቶች ልጆቻቸውን መቼ ነው የሚያሳድጉት? አንዳንዴ አለፍ አለፍ እያለ ልጆቹ እናቶቻቸውን ሲጠሩ እንሰማለን። እዚያ የሚሰቃየውም ልጅ ኢትዮጵያዊ ነውና ልናስብበት አይገባም ? አንዳንድ ግለሰቦች ቀን ተሌት ፓልቶክ ላይ ተሰክተው አንዱን ሲያሞግሱ አንዱን ሲሰድቡ ነው የሚኖሩት። በተጨማሪ በመጥፎ ወንጀል የሆነ ሱስ ተጠምዶ በተቃዋሚው ካንፕ መገኘት ከጥቅሙ ጉዳቱ ነው የሚያመዝነው። ስለዚህም አንዳንዴ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን እንደዚህ አይነት ቦዘኒያዊ ጠባይ ያላቸውን ግለሰቦች ከተቻለ መምከርና መመለስ ካልተቻለ ግን ከክፍሉ ማባረር የሚሻል ይመስለኛል። አልፈው ተርፈው አንዳንድ ጠቃሚ በሆኑ ስብሰባዎች ላይ መገኘታቸው ደግሞ ከወዲሁ ለወያኔ ዱላ እንደማቀበል ነው። እነዚህን „ተቃዋሚዎች“ ወያኔ ሲብስበት እጅ ከፍንጅ ከነወንጀላቸው አሲዞ ተቃዋሚው ሁሉ ወንጀለኛ ነው የሚሰኝን።

5ኛ. ሌላው በፓልቶክ ጎልቶ የሚሰማው የግንቦቱ ድል የሚለው ነው። ከግንቦቱ ድል እኩል የግንቦቱ ስህተት ለምን እንደማይጠቀስ አላውቅም። እኔ በበኩሌ የዴሞክራሲ ግማሽም አለ ብዬ አላምንም። የግንቦቱ ምርጫ ከመደረጉ በፊት የግንቦቱ ስህተት እንደተፈፀመ ለኔ ግልጽ ነው። አስመራጭ ኮሚቴው ላይ ሳንደራደር ፣ በምርጫው እንዳይሳተፉ የተከለከሉት ድርጅቶች እንዲሳተፉ እንዲፈቀድ ሳንጠይቅ ፣ የታሰሩ የጠፉ እስረኞችን ጉዳይ ሳንጠይቅ ፣ እንደው በደፈና የወያኔ „ዴሞክራሲያዊነቱን“ ለማሳየት ባዘጋጀው ቴያትር ውስጥ ተዋንያን ለመሆን ገብተን ሳለ የኢትዮጵያ ህዝብ ከትያትር በላይ ይገባኛል ብሎ ስለጠየቀና በወያኔ ላይ ያለውን ጥላቻ ስላሳየ ብቻ ስለግንቦት ድሉ አውርተን የግንቦት ስህተቱን ሳንናገር ማለፍ የለብንም። ለመሆኑ በስህተት ላይ የተመሰረተ „ዴሞክራሲ“ ውጤቱ ፋሺስዝም እንደሆነ ሊዘነጋ ይገባል? የምርጫውን ሂደት ለመቃወም ግልብጥ ብሎ ወያኔን ለመቃወም የወጣውን ህዝብ የኛ ህዝብ አደለም ብሎ መካድስ ስህተት አደለም ሊባል ነው? ወይስ ወያኔ እንዳይከሰን መረጃ እንዳያገኝ ያደረግነው ታክቲክ? እኛ ካድን አልካድን ወያኔ እንደሆነ ምክንያት ፈጥሮ ስለሚያሰር መረጃም አያስፍልገውም ነበር።ይህ ይባስ ተብሎ ደግሞ መሪዎቻችን ይፈቱ የሚለው ስህተት ነው። መሪዎቻችንን ያልሆኑትስ ? ስማቸው የማይታወቀውስ? ከግንቦቱ ስህተት በፊት የታሰሩትስ? ወይስ እነርሱ አመራር ውስጥ የሉምና አይፈቱ ነው?

እኔ በበኩሌ የግንቦቱ ድል ከግንቦቱ ስህተት በኃላ የመጣ ስለሆነ ወያኔ ያደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው። ገድሎአል ፣አስሮአል ፣ አጥፍቶአል። የግንቦቱ ድል የግንቦቱ ግርግር ውጤት ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ ሰዎች ህይወታቸውን የገበሩበት ለምሳሌ እንደነ ፕሮፌሰር አስራት ፣ እንደነ ጋይም ፣ እንዲሁም ብዙ ብዙ ሌሎች የተሰውበት ትግል ውጤት ነው። በወያኔ ከምርጫው ወዲያ የተደረገው ጭፍጨፋ ግን ስለወያኔ ምንነት እየተነገራቸው ካላየን አናምንም በሚሉ ግለሰቦች የተደረገ የግንቦቱ ስህተት ነው።

6ኛ. በሌላ በኩል ከሁሉም የሚገርመኝ ስሞኑን በፓልቶክ እንደበጋ ዝናብ እየተጣደፈ ቀርቦ የነበረ አሳብ ነው። ይኸውም በግንቦቱ የተገኘውን ድል ትተን እስረኞቹ እንዲፈቱ እንጠይቅና ለሚቀጥለው ምርጫ ከወያኔ ጋር እንደራደር የሚል

መግለጫ ለማውጣት በግለሰብ ደረጃ ቀርቦ የነበረው አሳብ(የድርጅትም ድጋፍ አያጣም) በብዙዎቹ በቅድሚያ በመምህራን ማህበር ተቃዋሚነት መክሸፉ ነው። በፓልቶኮች አካባቢ ለወያኔ ትግሉን መሰዋትነት ለማቅረብና በምዕተ አመት አመካኝተው ቦታ ለማግኘት መራወጡ እየጎላ ሲሆን የአድርባዩ ብዛትም ክፍ ብሎል።የሚገርመው ግን ይህንን ከላይ የጠቀስኩትን መግለጫ ያቀረቡት ግለሰቦች መርዙን በማር ለውስው ስላቀረቡት ብዙዎችን አወናብደዋል። ብልጥ አንዴ ነው እና የሚታለል ከአሁን በኃላ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

7ኛ. የወያኔ ደጋፊ የሆነው የሲቪሊቲ ክፍል ዛሬ የሞት ሽረት ትግል ይዞአል።የወያኔ ሚድያዎችም ሆኑ የውጭ አቀንቃኞቻቸው ኢኮኖሚውን አሳድገው አሳብጠው ሊፈነዳ አድርሰውታል።እኔ ያለኝ ልምድ ብዙዎቻችሁም እንደምታውቁት እንደ አዜውም 80 የልደት በዓል ካለፈ በኃላ የወሎ ድርቅ፣ ከደርግ 10ኛ ያብዮት በዓል የትግራይና የወሎ ድርቅን ነው የሰማነው። አዜው አገራችን የዳቦ ቅርጫት ነች ብለው ሲነግሩን ደርግ ደግሞ የአብዮቱን ፍሬ በፕሮፓጋንዳ ሲያስለቅመን ነበር። ትረሱት እንደሆን እንጃ እንጂ መንግስቱ ሀይለ ማርያም እንደ ጋቦንም ሳያንስ እንደ ሳውድ አረቢያም ሳይትረፈረፍ በቂ ቤንዝል ተገኝቶአል ብሎን ገንዝብ በገንዘብ መሆናችንን እያለምን ስንጨፍር የከረምነው የቅርብ ትዝታችን አደለም እንዴ?

የአገሪቱ እድገት ከሚደረገው በዓል በፊት ሁል ጊዜ እንዳደገ ነው። ዘንድሮም ከሚሊየሙ በፊት  የሚነገረን ይህንኑ ይመስላል።ጤፍ ዋጋ  ሃያ ሰባት በመቶ ባደገበት አገር ፣የስራ አጡ ቁጥር በሞላበት ሁኔታ ፣ የመንገድ ተዳዳሪው ቁጥር ሰማይ በደረሰበት ግዜ ፣ ይህ የወያኔ የሚለው እድገት ከምን ጋር ተወዳድሮ እንደሆነ አንደኛ የወጣው ግራ ነው የሚገባኝ። እንዳለፉት ሁለት መንግስቶች ከበዓሉ በኃላ ከሚመጣው ይሰውረን እላለሁ። ነገር ግን አሁንም ቢሆን እንዲህ አደገች ተመነደገች የሚሉን አገር በእርዳታ እህል እንደምትገኝ መደበቃቸው ነው የሚገርመኝ።ከሚሊየሙ በፊት ሁለቱ የቀደሙት መንግስታት እንዳደረጉት የጎዳና ተዳዳሪዎችን እያፈሱ ቀድሞ በተዘጋጁት እስር ቤት ውሰጥ እንደሚያጉሩዋቸው እምነቴ ነው።

ለግዜው ሚሌኒየሙን ለማክበር የምትሄዱትን መለስ ሆቴል እንዳትይዙ ለውጭ አገር ዜጎች እፈልገዋለሁ ስላለና ስላዘዛችሁ አሁን እንኳ ለብዙ ዘመናት ስትመላለሱ ያልጠየቃችኋቸውን ዘመዶቻችሁን ለመጠየቅ ግዜ ታገኛላችሁ በዛውም የአለቃችሁን ትእዛዝ ታከብራላችሁ። አደገ የተባለውንም ኢኮኖሚ ለማየት እድል ይገጥማችኃል። በተረፈ ለወያኔ ህዝቡ ያለውን ፍቅርም ታዩታላችሁ። የሚሳዝነን ግን የቤተሰብ ሳይሆን የወያኔ ፍቅር ከቤተሰቦቻችሁ ሊያገናኛችሁ ነው። የሚያይ አይን የሚስብ አዕምሮ ይሰጣችሁ ዘንድ የዘወትር ፀሎቴ ነው።

ስለኛ የሚያስብ በሰላም ይክረም!!!!

በልጅግ አሊ